# የካቲት ሲወሳ ወጣቱ  አይረሳ

*ካላንበት ወያኔያዊ ፅልመት ልንላቀቅ የምንችለው ተግባራዊ ተሳትፎን ያካተተ ትግል ማካሀድ ሲቻል ነው::  ከወይኔ ሌላ አልሰማ ላሉ ባዕዳን ሃይሎችም  የህዝብን ክብደት ልናስተምራቸው የምንችለው በተግባራዊ ትግል እንጂ በምለላ እንዳልሆነ መቀበል ይገባል:: ህዝብን አስተባብሮ ከህዝብ ጎን ሆኖ ለህዝብ ከመታገል ፈንታ ሰላማዊ ትግል እየተባለም እጅን አጣጥፎ " እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው" ፣ "ኤሎሂ! ኤሎሂ ! ፕርዜዳንት ኦባማ!  ከ ወያኔ/መለስ አገዛዝ ነፃ አውጥተህ እኛን እቀፈን" የሚሉ  ከበዙ አገር ከወያኔ ጥፋት ህዝብ ከውርደት አይድኑም::*

*የዲፕሎማሳዊው ጠቀሜታ እንዳለ ሆኖ፣ ይህም ትግል አቅጣጫና ሚዛን እንዲኖረው ህዝብ በስፋት በህዝባዊ ድርጅቶች ፣ በሙያ ማህበራት፣ በአርሶ አደሮች፣  በወጣቶች፣ በሴቶች ወዘተ በተግባር ሠላማዊ ትግል የሚጠይቀውን መስዋእትነት እየከፈለ እንዲታገል ማድረግ ሲቻል ነው:: ያኔም ነው እንደፍልስጤሞችና የደቡብ አፍሪካ ህዝብ  የዲፕሎማሲ ትግሉ ፍሬ ሊያፈራ የሚችለው::*

የህብረተሰቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች በውል ተጢነው በሰላምና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እስካልተፈቱ ድረስ ይዋል ይደር እንጂ ማህበራዊ ቅራኔዎች ፈጥጠው መውጣታቸው የማየቀር ለመሆኑ  ታሪክ ምስክር ነው:: ትግል    ፣   ትግል የሚሆነው በህብረተሰቡ ተ ሳትፎ በተለይም የነገውን ለውጥ ጎዳና ይመለከት ዘንድ ቀድሞ መስዋዕትነትን ለመክፈል ዝግጁ የሆነው በድፍርትም ከህዝብ ጠላቶች ጋር ለመጋፈጥ ግንባሩን የማያጥፈው አዲሱ ትውልድ በትግሉ በግንበር ቀደምትነት መሰለፍ ሲችል ነው:: የህብረተሰብ ታሪክም ለወጣቱ ትውልድ ይህንን ለህዝብ ጠላቶች መቅሰፍት የመሆን ሃላፊነትን ስጥታዋለች:: በ ኢትዮጵያ ትግል ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያ ወጣቶች በቆራጥነትና በጀግንነት ያጌጠ ምራፍ ይዘዋል:: ከ ኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የፈለቀው አዲስ ትውልድ ትናት በህብረተሰቡ ውስጥ ስር ሰደው የነበሩትን ቅራኔዎች በድፍረት መዞ እንዳወጣቸው ሁሉ ዛሬም ተመሳሳይ የታሪክ አደራ ተጥሎበታል::

ትናት ወጣት ተማሪዎች መሬት ላራሹ፣ ድህነት ወንጀል አይደለም ፣ ዳቦ ለተራበው የዲሞክራሲ መብቶች ይከበሩ ፣ ህዝባዊ መንግስት ይመስረት በማለት ፀረ- ጨቋኝ የዘውድ አገዛዝንና በፀረ ፋሽስት የትግል መድረክ ላይ ቀድመው ያመፅን ችቦ አቀጣጥለዋል:: ይህ ትግል በሚጠይቀው ከባድ መስዋዕትነት ከቶም ሳይበገሩ በብዕርና በድጋይ ብቻ ታጥቀው በነበረበት ጊዜ እንኳን ያለሰለሰ ትግል አካሂደዋል:: በዚህ ምክንያት ቅድመ የካቲት ኢትዮጵያ የኩሩ ወጣቶች እንቅስቃሴ ባለ ታሪክ ነች:: ወጣቱ ትውልድ የ አዲስ ዓለም አካል ነው:: አዲስ ነገር አፍላቂ፣ አዲስ ብልሃት አመንጪ ፣አዲስ ዕውቀት ተቀባይ በመሆኑ የዲሞክራሲ መብቶች መከበር፣ የህዝብ

መንግስት ምስረታ በተለይ በዩኒቨርሲቲ አካባቢ ነበሩትን ወጣት ምሁራን ህሊና ሰለማረከው በጭሰኝነት፣ በረሃብና በደዌ ለሚቆራመዱት አርሶአደሮች፣ በዘመናዊ የ እርሻ ተቋሞችና እንዱስትሪዎች ውስጥ አድካሚ ሥራ እየሰሩ አላግባብ ለሚበዘበዙት ላብ-አድአች መድህን ለመሆን በአጠቃላይ በፈላጭ ቆራጮች ፍዳውን ለሚያየው ብዙሃን ህዝብ ብሶት ከፍ አድርጎ በማሰተጋባት ታግለዋል :: ይህ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ትግል እንዲቀጣጠል ራሳቸውን አሰልፈው ለመስጠት የፈቀዱ ወጣት ተማሪዎችና ምሁራን በፖለቲካው መድረክ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆነዋል::

የኢትዮጵያ ወጣቶች እንቅስቃሴ በአሻፈረኝ ባይነት ብቻ አልተወሰነም:: ለቀመሉት ህዝባዊ ትግል መጠናከር ትክክለኛውን ጎዳን ለመቀየስ የበቁ በዚህም መራራና አስቸጋሪ ጉዞ ላይ የመጀመሪያዎቹን ዱካዎች በደማቸው ያተሙ ቆራጥ ታጋዮችን አፍርቷል:: ጊዜና ችሎታቸው በፈቀደው ዘዴ ተጠቅመው ፈለጋቸውን ተከትሎ የተመመው ታጋይ ትውልድ የሚጓዝበት አቅጣጫ ከተበጻዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍልጎትና የማህበራዊ ኑሮ ለውጥ ጋር ለማሰተባበር ከፍ ያለ ጥረት የአደረጉ የወጣት እንቅስቃሴ አካላት ከዚህ የሚመደቡ ናቸው::

" ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ!
በዱር በገደሉ ትግሉን እንድትመራ!
ነፃነትን እርነትን ለምትሸ!
ተዋጉለት አትሽሹ !"

ነበር የወቅቱ የትግል ጥሪና ዝማሬ :: የለውጥ እንቅስቃሴ ተቀጣጥሎ የነበረው በአገር ቤት ብቻ አልነበረም:: ቀደም ብለው ለትምህርት የወጡና በተለያዩ ምክንያቶች በውጭ ይኖሩ የነበሩ እንዲሁም በ አገር ቤት በተማሪዎችና በተቀረው የህብረተሰብ ክፍል ላይ በሚካሄደው ስለላ ፣ እስራት፣ አፈናና ግድያ የተነሳ የተሰደዱ ወጣት ተማሪዎችም ህዘቡን የሚቀሰቅሱ ፅሁፎችን እያሰናዱ ወደ አገር ቤት በማስገባት ሰላማዊ ሰልፎችንና የረሃብ አድማዎችን በማድረግ ወዘተ የአገዘዙን ኢ-ፍትሃዊነት ለዓለም ህዝብ አጋልጠዋል:: ከትምህርቴ እተጓጎላለሁ፣ እታሰራለሁ፣ እንደወጣሁ እቀራለሁ ሳይሉ የግል ፍለጎታቸውን ለወገን ክብርና ለኢትዮጵያ ህዝብ ልዕልና ሲሉ ታግለዋል::

ይህ በወጣት ተማሪዎችና ምሁራን ተቀስቅሶ በከተማና በገጠር የተቀጣጠለውን የለውጥ እንቅስቃሴ አገዛዙ በለሆሳስ የተመለከተበት ጊዝ ቄኢም ችል ብሎ ያለፈበት ምንም ጊዜ

አልነበረም:: የስራ ማቆም አድማ ያደረጉ የሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ የወጡ ታጋዮች እንደተጋዙና እንደተረሸኑ ሁሉ ህዝባዊ ትግል አካል የሆነው እንቡጡ የወጣቶች እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩ ሁሉ የተጋረጠባቸው አደጋ ተመሳሳይ ነበር::

ከየካቲት 1966 ዓ.ም በፊትም ምንም እንካን ሰራ አውና የተማሪዎወች እንቅስቃሴ ከልልኦች ህብረተሰብ ከፍሎች ትግል የተሳለ ድርጅትዊ መልክ ቢይዝም ከሁሉም አቅጣጫ ትግሉን በማስተባበርና በግንባር ቀደምትነት የሚመራ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት አለመኖሩ በኢትዮጵያ የለውጥ ዕንቅስቃሴ ላይ ራሱን የቻለ አሻራ ጥሎ አልፋል:: ይህ በእንዲህ እንዳለ ነሀሴ 1967 ዓ.ም. የ ኢ. ሕ አ ፓ ይፋ መውጣት ለዚህ አንገብጋቢ የደርጅታዊ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በመቻሉ ለወጣቱና ለሌላው ታጋይ የህብረተስብ ከፍል ትልቅ የምስራች ነበር::

የ ኢትዮጵያ ወጣቶች አማባገነንነትን ለመቋቃም ያደረጉት ትግል ከ ኢሕአፓ ጎን ተሰልፈው ጭቆናን መፋለማቸው ዘወትር ሲታወስ የሚኖር፣ ትውልድን የሚያኮራ ተግባር ነው:: በዚህ ፈጣን የትግል እንቅስቃሴ ውስጥ ግንብራቸውን ሳጥፉ ነፃነትን ብርሃን ፍለጋ ሳያወላውሉ ቆርጠው የተነሱን ለተከታዩ ትውልድ ሥነ-ምግበር አርአያና ጀግንነት ምሳሌ የሚሆኑ ብርቅዬ ወጣት ታጋዮች ተሰውተዋል:: የካቲትን ስንዘክር እነዚያን በ አራቱም ማዕዘናት ኢትዮጵያን ባጥለቀለቀው ህዝባው አመፅ ከተበዳዩ የ ኢትዮጵያ ህዝብ ጎን የተሰለፉ ወጣት ታጋዮችን ገድል ምንም አይነት ሃይል ከታሪካችን ውስጥ ሊፍቀው አይችልም::
ያለፈው ትውልድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉኣላዊነት ተጠብቆ መቆየት የፈፀመውን ገድልና የዛሬውም ወጣት ትውልድ ለነፃነትን ለፍትህ የወደቁ ወንድሞቹንና እህቶቹን ፈለግ ተከትሎ የትግል ሰንደቃቸውን ካረፈበት በማናሳት ረጅም መንገድ ቀድሞአቸው መጓዝ ይጠበቅበታል::

ወጣቱ ዛሬም ለጎጠኞችና ለአምባገነኖች ጠር ነው!!!